# የጤናው ዘርፍ የ2012 በጀት አመት
# የመልካም አስተዳደር መሪ ዕቅድ

ነሐሴ 2011 ዓ.ም

## 1. መግቢያ

በጤናዉ ዘርፍ ልማት የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ባለፉት አመታት በርካታ ዉጤታማ ሥራዎች ተከናዉነዋል፡፡ በጤና ተቋማት ግንባታ፣ በሰዉ ሃይል ስልጠናና ስምሪት፣ የግብአት አቅርቦትና ቁጥጥር ሥርዓቱን በማሻሻል ረገድ ሰፋፊ ሥራዎች ተሰርተዋል፡፡ ይሁን እንጂ በጤና አገልግሎት ተደራሽነትና ጥራት እንዲሁም በግብአት አቅርቦት ዙሪያ በህብረተሰቡ የሚነሱ በርካታ ቅሬታዎች አሁንም መኖራቸዉ የሚካድ አይደለም፡፡ ከዚህም በመነሳት የጤና አገልግሎት ጥራትና ፍትሃነትን ማረጋገጥ የጤናዉ ዘርፍ ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ቁልፍ አጀንዳ እንዲሆን ተደርጓል፡፡

የጤና አገልግሎት ጥራትና ፍትሃዊ ተደረሰሽነትን በማሻሻል የተገልጋዩን ህብረተሰብ እርካታ ለማረጋገጥ በየደረጃዉ የሚታዩ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በተቀናጀ አሰራር መፍታትን ይጠይቃል፡፡ በጤና ተቋማት የሚገኘው የሰው ሃይል ተገልጋዮችን በአክብሮትና በርህራሄ ከማስተናገድ አንፃር የሚታዩ ጉድለቶች፣ በግዥና የሎጂስቲክ አስተዳደር ዙሪያ የሚታዩ ችግሮች መቀረፍ ይኖርባቸዋል፡፡

ከዚህም መበነሳት ከጤና ሚኒስቴር፣ ከተጠሪ ተቋማትና ከክልል ጤና ቢሮዎች የተወጣጡ የሪፎርምና መልካም አስተዳደር እንዲሁም ሌሎች የሥራ ክፍሎች የተወጣጡ ባለሙያዎችና የሥራ ሃላፊዎች በተገኙበት የጤናው ዘርፍ የ2012 በጀት አመት የመልካም አስተዳደር መሪ ዕቅድ ተዘጋጅቷል፡፡ ዕቅዱን ከወረዳ ጀምሮ እስከ ፌዴራል ባሉ መዋቅሮች እንደየተጨባጭ ሁኔታቸው ተግባሪዊ በሚደረግ መልኩ ለማዘጋጀት ተሞክሯል፡፡

## 2. መነሻ ሁኔታዎች

የጤናው ዘርፍ የ2012 በጀት የመልካም አስተዳደር ዕቅድ እንደ መነሻ የተወሰዱት ባለፈው በጀት አመት በተለያዩ የውይይት መድረኮች የተነሱ ሃሳቦችና የሱፐርቪዥን ሪፖርቶች ናቸው፡፡ በ2011 ዓ.ም የተካሄደው የተቀናጀ ድጋፋዊ ክትትልና ኢንስፔክሽን ሪፖርት፣ በአራት ማዕከላት በተካሄዱ የኮር አመራር ስልጠና መድረኮች የተነሱ ሃሳቦች፣ በ22 የዩኒቨርሲቲና የፌዴራል ሆስፒታሎች የተካሄደው የመልካም አስተዳደር ኢንዴክስ ዳሰሳ ሪፖርት በዋናነት የተወሰዱ የዕቅዱ መነሻዎች ናቸው፡፡ በተጨማሪም ከጤና ሚኒስቴር የተሳተፉ የተለያዩ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክሬክተሮች፣ ከተጠሪ ተቋማት ከክልሎች የተሳተፉ የሪፎርምና መልካም አስተዳደር መዋቅሮች ሃላፊዎችና ባለሙያዎች ያነሷቸው ሃሳቦች እንደ ተጨማሪ ግብአት ተወስደዋል፡፡

## 3. የመልካም አስዳደር ችግሮች ልየታና የክብደት መለኪያዎች

በሀገራችን በየደረጃው ባለው የመንግስት መዋቅር በከተማም ይሁን በገጠር መልካም አስተዳደርን ለማስፈን ያስችላሉ ተብለው የተወሰዱ ስምንት የመልካም አስተዳደር መርሆዎች ተለይተዋል፡፡ እነሱም የህግ የበላይነት፣ ተጠያቂነት፣ ተሳትፎአዊነት፣ ግልጽነት፣ ቶሎ ምላሽ መስጠት፣ ቅልጥፍናና ውጤታማነት፣ የጋራ መግባባት እና ፍትሃዊነት ናቸው፡፡ ስለሆነም በየደረጃው የሚከሰት ማንኛውም የመልካም አስተዳደር ችግር እነዚህን መረሆዎች በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ ካለማድረግ የሚመነጭ አስተዳደራዊ ችግር ነው፡፡

በዚሁ መሰረት ከላይ ከተጠቀሱ የመልካም አስተዳደር መረሆዎች አንፃር የመልካም አስተዳደር ችግሮችን የመለየት ሥራ የተሰራ ሥራ ሲሆን ከተለዩ ችግሮች መካከል ቅድሚያ የሚሰጣቸውን በአራት ዋና ዋና መስፈርቶች በመገገም በዕቅድ የሚካተቱት ተለይተዋል፡፡ አራቱ መስፈርቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

| ተ.ቁ | የመመዘኛ ነጥብ | ማብራሪያ |
|---|---|---|
| 1 | እርካታ የመፍጠር ተጽዕኖ | ችግሩ በመሰረታዊ ባህሪይው ከአገልግሎት ተጠቃሚው ዜጋ ጋር ያለውን ቀጥተኛ ትስስር፣ ችግሩን መፍታት የዜጎችን እርካታ ከማሳደግ አንጻር የሚኖረውን ድርሻ እና ችግሩ በአባዛኞቹ መርሆዎች መጣስ ምክንያት የተፈጠረ ስለመሆኑ |
| 2 | ገዥነት | ችግሩ በመሰረታዊ ባህሪይው ቁልፍ የሆነ፣ ከብዙ ጉዳዮች ጋር የተያያዘ፣ችግሩን በመፍታት ምክንያት ሌሎች ተያያዥነት ያላቸውን ችግሮች ለመፍታት የሚያስችል እና ችግሩ በበርካታ መርሆዎች መጣስ ምክንያት የተፈጠረ ስለመሆኑ |
| 3 | አንገብጋቢነት | ችግሩ ፈጣን ምላሽ የሚሻ፣ በወቅቱ ካልተፈታ ለተጨማሪ ወጪ የሚዳርግ እና የችግሩ መፈታት ለሌሎች ችግሮች መፈታት በቅድመ ሁኔታነት የሚታይ ስለመሆኑ |
| 4 | የሚያስከትለው አደጋ | ችግሩ ካልተፈታ ዜጎች በአገልግሎት ሰጪው ተቋምና በመንግስት ላይ በቀጣይ በሚኖራቸው አመኔታ ላይ የሚፈጥረውን አሉታዊ ተፅዕኖ እና ይህ ሁኔታም በአገልግሎት ሰጪው ተቋም ህልውና እንዲሁም በአገር ደረጃ የሚኖረውን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ አንደምታን የሚዳስስ ነው፡፡ |

ከላይ የተዘረዘሩ የመልካል አስተዳደር ችግሮች መመዘኛ መስፈርቶችን መሰረት በማድረግ ቁልፍ የሆኑ የመልካም አስተዳደር ችግሮች የተለዩ ሲሆን ለክትትልና ድጋፍ እንዲያመች በዘርፍ በዘርፍ እንዲመደቡ ተደርጓል፡፡ በዚህም መሰረት የተለዩ የመልካም አስተዳደር ችግሮች በሰባት ዘርፎች የተመደቡ ሲሆን እነሱም፡-

- በመሰረታዊ የጤና አገልግሎት ደረጃ የተለዩ
- በጤና አገልግሎት አሰጣጥ ዘርፍ የተለዩ
- በመድሃኒትና የህክምና መሳሪያዎች አቅርቦት ዘርፍ የተለዩ
- በጤና ቁጥጥር ሥርዓት ዘርፍ የተለዩ
- በሰው ሀይልን በሀብት አስተዳደር ዘርፍ የተለዩ
- በጤና ፕሮግራሞች አመራር ላይ የታዩ
- የጤና መረጃ ሥርዓትን የተመለከቱ ናቸው

ከላይ በተዘረዘሩ ምድቦች የተለዩ የመልካም አስተዳደር ችግሮች፣ የችግሮቹ መንስኤዎች፣ የመፍትሄ ሃሳቦች፣ የሚመለከታቸው አካላትና እና የአፈፃፀም ውጤት መለኪያዎች ትንተና እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

## 4. የመልካም አስተዳደር ችግሮች፣ መንስኤዎችና የመፍትሄ ሃሳቦች ትንተና ማትሪክስ

| ተ.ቁ | የመልካም አስተዳደር ችግር | የችግሩ መንስኤዎች | የመፍትሄ ሃሳች | ፈፃሚ | የውጤት መለኪያዎች |
|---|---|---|---|---|---|
| 1. በመሰረታዊ የጤና አገልግሎት አሐድ ደረጃ | | | | | |
| 1.1 | የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ውጤታማነት እየቀነሰ መምጣት | የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች የሚነሱ የተለያዩ ቅሬታዎች ወቅታዊ ምላሽ አለማግኘት | የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች ምደባና ዝውውርን በሲቪል ሰርቪስ መመሪያ መሰረት ተግባራዊ ማድረግ | ክልሎች | በመመሪያው መሰረት ተግባራዊ ያደረጉ ክልሎች ብዛት |
| | | | ግልጽ የሆነ የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች የትምህርት ደረጃ ማሻሻያ ሥርዓት ተግባራዊ ማድረግ | ክልሎች፣ ጤና ኤክ/መስ/ጤና አገ/ ዳይ/ሬት | ተጠቃሚ የሆኑ የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች ብዛት |
| | | ወደ ህክምና አገልግሎት ያደላ የህብረተሰቡ ፍላጎት እያደገ መምጣት | የ2ኛ ትውልድ የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ትግበራ ማጠናከር | ክልሎች፣ ጤና ኤክ/መስ/ጤና አገ/ ዳይ/ሬት | ትግበራ የጀመሩ ጤና ኬላዎች ብዛት |
| | | ለጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች በሚሰጡ ተደራራቢ ተልዕኮች ምክንያት የሚፈጠር የሥራ ጫናና መሰላቸት | የማይመለከታቸውን ተደራራቢ ተልዕኮዎች ማስቀረት | ክልሎች | ማስተካከያ ያደረጉ ወረዳዎች ብዛት |
| | | | እጥረት ባለባቸው አካባቢዎች የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች ቁጥር መጨመር | ክልሎች | አዳዲስ የተቀጠሩ የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች በቁጥር |
| | | በጤና ኬላዎች የሚያስፈልጉ ግብአቶች ተማልተው አለመገኘት | አስፈላጊ የሆኑ ግብአቶችን ማሟላት | መ/አ/ኤ/ ፣ ክልሎች | የተሟላ ግብአት |
| | | የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም የአፈፃፀም መመሪያ ወጥነት ባለው ሁኔታ አለመፈፀም | ለአርሶ አደር፣ ለአርብቶ አደር እና ለከተማ አካባቢዎች እንደ ነባራዊ ሁኔታቸው ወጥ የሆነ አሰራር ተግባራዊ ማድረግ | ጤና ኤክ፣ ልዩ ድጋፍ ዳ/ሬቶች | ተግባራዊ ያደረጉ ክልሎች |
| | | የአመራሩ ድጋፍና ክትትል እየቀነሰ መምጣት | የንቅናቄ ሥራ | ጤና ኤክ፣ ልዩ ድጋፍ ዳ/ሬቶች፣ ክልሎች | እስከ ቀበሌ ንቅናቄ ያካሄዱ ክልሎች |
| 1.2 | ጤና ጣቢያዎች | የመድሃኒትና ህክምና | በስታንዳርዱ መሰረተደ ማሟላት | መ/አ/ኤ/ ፣ | ያሟሉ ጤና ጣቢያዎች ብዛት |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ለተገልጋዮቻቸው የተሟላ አገልግሎት መስጠት አለመቻል | መሳሪያዎች አለመሟላት | | ክልሎች | |
| | | የሰው ሃይል እጥረትና ክህሎት ማነስ | አስፈላጊውን የሰው ሃይል መማሟላት | ክልሎች | በስታንዳርዱ መሰረት ያሟሉ ጤና ጣቢያዎች ብዛት |
| | | | የክህሎት ማሻሻያ ስልጠናዎች መስጠት | ክልሎች | የክህሎት ስልጠና የሰጡ ጤና ጣቢያዎች |
| | | | ክሊኒካል ጋይድላይን ማዳረስና መተግበር | ጤና ኤክ፣ ልዩ ድጋፍ ዳ/ሬቶች | ተግባራዊ ያደረጉ ጤና ጣቢያዎች |
| | | የተሟላ መሰረተ ልማት አለመኖር | በተሸሻለው ዲዛይን መሰረት ግንባታ ማስፋፋት | ጤና መሰረተ ልማት ክልሎች | በተሻሻለው ስታንዳርድ የተገነቡ ብዛት |
| | | | የውሃና ኤሌክትሪክ አቅርቦት ማዳረስ | ክልሎች | የተሟላላቸው ብዛት |
| | | በጤና ጣቢያዎች አመራርና አስተዳደር የህብረተሰቡ ተሳትፎ የተጠናከረ አለመሆን | የማህበረሰብ አስተያየት ምዘና ሥርዓትን ማጠናከር | ሪፎርምና መልካም አስ/፣ ክልሎች | የማህበረሰብ አስተያየት ምዘና ሥርዓትን ተግባራዊ ያደረጉ ጤና ጣቢያዎች ብዛት |
| 1.3 | የማህበረሰብ አቀፍ ጤና መድህን የተጠቃሚነት ሽፋንና የአመራር ሥርዓት ውጤታማ አለመሆን | የጤና መድህን ተቋማዊ አደረጃጀትና የሰው ሃይል ችግር | ወጥ የሆነና የጠራ መዋቅራዊ አደረጃጀት መፍጠር | ጤና መድህን ኤጀንሲ፣ ክልሎች | ተግባራዊ የተደረገ መዋቅር |
| | | | አስፈላጊውን የሰው ሃይል ማሟላት | ጤና መድህን ኤጀንሲ፣ ክልሎች | የተሟላ የሰው ሃይል በመቶኛ |
| | | አገልግሎት ያልጀመሩ ክልሎችና ወረዳዎች መኖር | እንዲጀምሩ አስፈላጊውን ድጋፍና ክትትል ማድረግ | ጤና መድህን ኤጀንሲ፣ ክልሎች | አገልግሎት የጀመሩ ወረዳዎች በቁጥር |
| | | መክፈል የማይችሉ የህበረሰብ ክፍሎች ተጠቃሚ ከማድረግ አኳያ ወጥ የሆነ አሰራር አለመኖር | በየደረጃው በመንግስት በጀት የሚያዝበትና የልየታ አሰራር ሥርዓት መዘርጋት | ጤና መድህን ኤጀንሲ፣ ክልሎች | መመሪያውን ተግባራዊ ያደረጉ ወረዳዎች በቁጥር |
| | | የማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድህን አተገባበር የህግ ማዕቀፍ አለመኖር | ረቂቅ አዋጁን በአጭር ውስጥ በማፀደቅ ተግባራዊ ማድረግ | ጤና መድህን ኤጀንሲ፣ ክልሎች | ፀድቆ ተግባራዊ የተደረገ አዋጅ |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | የአመራር ቁርጠኝነትና የግንዛቤ እጥረት መኖሩ | ተከታታይ የሆኑ የጋራ ውይይቶችና የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራዎችን መስራት | ጤና መድህን ኤጀንሲ | የተደረጉ የጋራ ምክክር መድረኮች ብዛት |
| 2. የጤና አገልግሎት አሰጣጥ | | | | | |
| 2.1 | በጤና ተቋማት የአገልግሎት ጥራትና ቅልጥፍና መጓደል ምክንያት የሚፈጠር የተጠቃሚዎች እርካታ ማነስና እንግልት መኖሩ | የህክምና ግብአቶች አለመሟላት | የመድሃኒት አቅርቦት ማሻሻል | መድሃኒት አቅርቦት ኤጀንሲ | የመድሃኒት አቅርቦት ምጣኔ በመቶኛ |
| | | | የህክምና መሳሪያዎች አቅርቦትና የአጠቃቀም አቅም ማሻሻል | መድሃኒት አቅርቦት ኤጀንሲ፣ PMED | የህክምና መሳሪያዎች በስታንዳርድ መሰረት ያሟሉ ተቋማት ምጣኔ በመቶኛ |
| | | | የኬሚካሎችና ሪኤጀንቶች አቅርቦት ማሟላት | መድሃኒት አቅርቦት ኤጀንሲ | የአስፈላጊ ኬሚካሎችና ሪኤጀንቶች አቅርቦት ምጣኔ በመቶኛ |
| | | ከአቅም በላይ የሆነ የታካሚዎች ፍሰት በአገልግሎት የሚፈጥረው ጫና | የሪፌራል ሥርዓቱን ውጤታማ ማድረግ | ክሊኒካል አገ/ ፣ ክልሎች | አግባብነት ያላቸው ሪፌራሎች መጠን በመቶኛ |
| | | | የታችኞቹን የጤና ተቋማት አቅም ማጠናከር | ክልሎች | ወደ ሌሎች የሚላክ ሪፌራል መቀነስ በመቶኛ |
| | | በተለያዩ የሙያ መስኮች የሰው ሃይል አለመሟላትና የክህሎት እጥረት መኖሩ | እጥረቶች ባለባቸው የሙያ ዘርፎች የስልጠና ፕሮግራሞች ማካሄድ | የሰው ሀብት ልማት ፣ ክልሎች | ወደ ስልጠና የገቡ ባለሙያዎች ብዛት በቁጥር |
| | | | የሥራ ላይ ስልጠና (CPD) ማጠናከር | የሰው ሀብት ልማት ፣ ክልሎች | በCPD ስልጠና የተሳተፉና የተመዘኑ ባለሙያዎች ብዛት |
| | | የጤና ባለሙያዎችና ሌሎችም ሰራተኞች የአገልጋይነት መንፈስ መጓደል | የCRC ንቅናቂ በአዲስ መልክ ማጠናከር | የሰው ሀብት ልማት ፣ ክልሎች | በተገልጋዮች እርካታ የታየ መሻሻል በመቶኛ |
| | | | የተጠያቂነት አሰራር ማጠናከር | ጤና ሚኒስቴር፣ ክልሎች | የእርምት እርምጃ የተወሰደባቸው ሰራተኞች ብዛት |
| 2.2 | በድንገተኛ ህክምና | የድንገተኛ ህክምና መስጫ | የድንገተኛ ህክምና ክፍሎችን | ድንገተኛና ጽኑ | የተሟላ ድንገተኛ ህክምና |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | አገልግሎት ጥራትና ውጤታማነት መጓደል በታካሚዎች ላይ የሚደርስ ጉዳት መኖሩ | ክፍሎች ከደረጃ በታች መሆን | በስታንዳርዱ መሰረት ማጠናከር | ህሙማን ዳ/ሬት፣ ክልሎች | መስጫ ክፍሎች ያሏቸው ተቋማት ብዛት |
| | | በድንገተኛ ህክምና ዘርፍ የሰለጠኑ ባለሙያዎች እጥረት | የድንገተኛ ህክምና ባለሙያዎች መደበኛና የሥራ ላይ ስልጠና ማካሄድ | የሰው ሀብት ልማት፣ ጤና ተቋማት | የክህሎት ስልጠና የወሰዱ ሰራተኞች ብዛት |
| | | በቂና ደረጃውን የጠበቀ የአምቡላንስ አገልግሎት አለመኖር | የአምቡላን አቅርቦትና ውስጣዊ አደረጃጀትን ማሻሻል | ጤና ሚኒስቴር ፣ ክልሎች | ውስጣዊ አደረጃጀታቸው የተሟላ አምቡላንሶች ብዛት |
| | | በቂ ፖሊትራኦማ ማዕከላት አለመኖር | በተለያዩ ክልሎች ፖሊትራኦማ ማዕከላትን መገንባት | ጤና ሚኒስቴር | ግንባታቸው የተጀመረ የፖሊትራኦማ ማዕከላት በቁጥር |
| 2.3 | የጤና ተቋማት ምቹና ደህንነታቸው የተጠበቀ አለመሆን ለተገልጋዮችና ለሰረተኛው የአደጋ ስጋት መሆኑ | ነባር ሆስፒታሎች ከመሰረተ ልማት አንፃር የስታንዳርድ ጉድለት ያለባቸው መቦናቸው | የማስፋፊያ ግንባታ የእድሳት ሥራዎችን ማከናወን | ጤና ሚኒስቴር፣ ክልሎች፣ ጤና ተቋማት | እድሳት የተደረገላቸው ተቋማት ብዛት |
| | | | | | የማስፋፊያ ግንባታ የተካሄደባቸው ተቋማት ብዛት |
| | | ለተቋማት ደህንነት (safity)፣ ጽዳትና ውበት በቂ ትኩረት አለመስጠት | የ CASH ትግበራ ማጠናከር | ክልሎች፣ ጤና ተቋማት | CASH በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ ያደረጉ ተቋማት ብዛት |
| 2.4 | በጤና ተቋማት አመራር ና አሰራር ድክመቶች ምክንያት ከተገልጋዮችና ከሰራተኞች የሚነሱ ቅሬታዎች መኖራቸው | የሆስፒታሎች የሥራ አመራር ቦርዶች አለመሟላትና ሃላፊነታቸውን በአግባቡ አለመወጣት | ውጤታማ የሆኑ የሥራ አመራር ቦርዶችን ማደራጀትና መደበኛ ስብሳባዎች በመመሪያው መሰረት ማካሄድ | ጤና ሚኒስቴር፣ ክልሎች፣ ጤና ተቋማት | የተካሄዱ የሥራ አመራር ቦርድ ስብሳባዎች በቁጥር |
| | | የአገልግሎት ማሻሻያ ሪፎርሞች በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ አለመሆን | የሪፎርሞችን ትግበራ በአመራር ደረጃ ትኩረት ሰጥቶ መከታተል | ጤና አገ/ ጥራት፣ ጤና ተቋማት | በአመራር ደረጃ በሪፎርሞች ትግበራ የተካሄደ ግምገማና ግብረ መልስ ብዛት |
| | | | የሪፎርሞች ትግበራ የሚከታተሉ መዋቅሮችን ማጠናከር | ክልሎች፣ ጤና ተቋማት | አስፈላጊው የሰው ሃይል የተሟላላቸው የሪፎርም መዋቅሮች ብዛት |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | በዕቅድ ዝግጅት፣ በአፈፃፀም ክትትልና ግምገማ ሰራተኛውን በተደራጀ ሁኔታ አለማሳተፍ | በተለያዩ ሪፎርሞች ትግበራና በሥራ ዙሪያ ከአጠቃላይ ሰራተኞች ጋር ውይይቶችን ቀጣይነት ባለው ሁኔታ ማካሄድ | ጤና ተቋማት | የተካሄዱ የአጠቃላይ ሰራተኛ ውይይት መድረኮች ብዛት |
| | | ውጤታማ የማህበረሰብ ተሳትፎና ባለቤትነት መፍጠር አለመቻል | የህዝብ ክንፍ መድረኮችን በየሩብ አመቱ በቂ ዝግጅት አድርጎ ማካሄድ | ጤና ተቋማት | የተካሄዱ የህዝብ ክንፍ መድረኮች ብዛት |
| | | የቅሬታና አቤቱታ ማስተናገጃ አሰራር አለመጠናከር | የቅሬታና አቤቱታ መቀበያ ክፍሎችን ማደራጀትና ምልሽ የመስጠት አቅም ማጠናከር | ጤና ተቋማት | ተገቢ ምላሽ ያገኙ ቅሬታዎች ብዛት |
| 2.5 | በዩኒቨርሲቲ ሆስፒታሎች በአገልግሎት አሰጣጥ ዘርፉ ላይ የሚነሱ በርካታ የውስጥና የውጭ ቅሬታዎች መኖራቸው | የዩኒቨርሲቲ አመራሮች ለስልጠና ዘርፉ ያደላና ለህክምና አገልግሎት ዘርፉ በቂ ትኩረት አለመስጠት | የዩኒቨርሲቲ ሆስፒታሎች በፋይናንስና በሰው ሃይል አስተዳደር እንደ አንድ ፌዴራል ተቋም ራሳቸውን ችለው እንዲዋቀሩ ማድረግ | ጤና ሚኒስቴር፣ ገንዘብ ሚኒስቴር፣ የከፍተኛ ትም/ት ሚኒስቴር | ራሳቸውን ችለው መተዳደር የጀመሩ የዩኒቨርሲቲ ሆስፒታሎች ብዛት በቁጥር |
| | | ከጤና ሚኒስቴር ጋር ያለው ቅንጅታዊ አሰራር አለመጠናከር | በተጠያቂነት ላይ የተመሰረተ የጋራ አሰራር ሥርዓት መፍጠር | ጤና ሚኒስቴር፣ ዩኒቨርሲቲዎች | በመልካም አስተዳደር ኢንዴክስ መለኪያ የታየ ለውጥ በመቶኛ |
| 2.6 | የጤና አገልግሎት ፍትሃዊ ተደራሽነት ጉድለቶች መኖራቸው | ከጤና ተቋማት ባላቸው ጂኦግራፊያዊ ርቀት ምክንያት ተደራሽ አለመሆን | ተደራሽ ባልሆኑ አካባቢዎች ተጨማሪ የጤና ተቋማት መገንባት | ጤና ሚኒስቴር፣ ክልሎች | የተገነቡ ተጨማሪ የጤና ተቋማት ብዛት |
| | | የስፔሻሊቲ አገልግሎቶች ተደራሽ አለመሆን | የስፔሻሊቲ ሀኪሞች ቁጥርና ተደራሽነት ማሳደ | ጤና ሚኒስቴር | በስታንዳርድ መሰረት የታየ መሻሻል |
| 3. የመድሃኒትና ህክምና መሳሪያዎች አቅርቦት | | | | | |
| 3.1 | ለጤና ተቋማት መድሃኒትና የህክምና መሳሪያዎችን በተሟላ ሁኔታ ማቅረብ አለመቻል | የፍላጎት ትንበያ ስርዓት ላይ የጥራት ችግር መኖሩ | አሳታፊና በመረጃ ላይ የተመሰረተ የትንበያ ሥርዓት ማጠናከር | የመድ/ህክ/ መሳ/ ዳይሬክቶሬት | የትንበያ እርግጠኝ ምጣኔ በመቶኛ |
| | | የግዢ ስርዓቱ ቀልጣፋ አለመሆን | የማዕቀፍ ግዥ አሰራርን መተግበር | የመድ/ አቅርቦት ኤጀንሲ | በማዕቀፍ የተፈፀመ ግዥ በመቶኛ |
| | | የስርጭት ስርዓቱ ቀልጣፋ | የክምችት አስተዳደርን ማዘመን | የመድ/ አቅርቦት | ዘመናዊ የክምችት ሥርዓት |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | አለመሆን | | ኤጀንሲ | ተግባራዊ ያደረጉ ቅርንጫፎች ብዛት በቁጥር |
| | | | የስርጭትና የማጓጓዝ ቅልጥፍናን ማሻሻል | የመድ/ አቅርቦት ኤጀንሲ | ወደ ጤና ተቋማት የማድረስ አማካይ ቆይታ በቀናት |
| | | ከጤና ተቋማት ጋር ያለው ቅንጅታዊ አሰራር ውስንነት | የቅርንጫፎችና የጤና ተቋማት የጋራ ፎረሞችን ማጠናከር | የመድ/ አቅርቦት ኤጀንሲ ቅርንጫፎች | የጋራ ፎረም በማቋቋም ተቀናጅተው የሚሰሩ ቅርንጫፎች ምዛት |
| 3.2 | ተገዝተው የተሰራጩ የተሰራጩ የህክምና መሳሪያዎች ተከላ መዘግየትና ከተተከሉ በኋላም በአግባቡ አገልግሎት አለመስጠት | በተቋማት ውስጥ ለተከላ የሚሆን ቦታ መሰረተ ልማት በወቅቱ አለመዘጋጀት | የህክምና መሳሪያዎችን ከማሰራጨት አስቀድሞች የተከላ ቦታና አስፈላጊ ዝግጅት መደረጉን ማረጋገጥ | የመድ/ አቅርቦት ኤጀንሲ | የተላኩ የህክምና መሳሪያዎችን በወቅቱ አስተክለው ሥራ ያስጀመሩ ተቋማት በመቶኛ |
| | | ከአቅራቢ ተቋማት ጋር በተገባው ውል መሰረት የመሳሪያዎች ተከላ ክትትል ውስንነት | አቅራቢ ተቋማት በገቡት ውል መሰረት ተከላ እንዲፈጽሙ ትኩረት ሰጥቶ መከታተል | የመድ/ አቅርቦት ኤጀንሲ | በተቀመጠው ጊዜ ውስጥ የተተከሉ መሳሪያዎች ብዛት |
| | | ዘመናዊ የህክምና መሳሪያዎች አያያዝና አጠቃቀም የክህሎት እጥረቶች መኖራቸው | የአጠቃቀምና አያያዝ ክህሎት ማጎልበቻ ማዕከላት (ወርክሾፖች) ማደራጀት | የመድ/ አቅርቦት ኤጀንሲ | የክህሎት ስልጠና የወሰዱ ባለሙያዎች ብዛት |
| 3.3 | የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው መድሃኒቶችና የህክምና መሳሪያዎች በወቅቱ ባለመወገዳቸው ለህብረተሰቡ ጤና የአደጋ ስጋት መሆናቸው | የተገነቡ የማቃጠያ ኢንስኔሬተሮች በአግባቡ ሥራ አለመጀመራቸው | የተገነቡ የማቃጠያ ኢንስኔሬተሮችን በተሟላ ሁኔታ ወደ ሥራ ማስገባት | የመድ/ አቅርቦት ኤጀንሲ | ሥራ የጀመሩ የማቃጠያ ኢንስነሬተሮች ብዛት |
| 4. የጤና ቁጥጥር ሥርዓት | | | | | |
| 4.1. | ደህንነታቸው ያልተጠበቀ ምግብና ምግብ ነክ ምርቶች | የቁጥጥር መላላትና በህገ ወጦች ላይ አስተማሪ | የግልፀኝነትና ተጠያቂነት አሰራርን ማጠናከር | ምግ/መድ/ ቁጥ/ ባለስልጣን፣ | በህገ ወጦች ላይ የተወሰዱ እርምጃዎች ብዛት |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | በገበያ ውስጥ መኖራቸው የህብረተሰቡ የጤና ጠንቅ እየሆነ መምጣቱ | እርምጃዎች አለመወሰድ | | ክልሎች | |
| | | በቁጥጥር ሥራው ህብረተሰቡን በባለቤትነት አለማሳተፍ | የንቅናቄ ሥራዎችን በተከታታይነት መስራት፣ | ምግ/መድ/ ቁጥ/ ባለስልጣን | የተካሄዱ የንቅናቄ መድረኮች ብዛት |
| | | | ጥቆማ የሚቀርብባቸውን አሰራሮች ማጠናከር | ምግ/መድ/ ቁጥ/ ባለስልጣን | ከህብረተሰቡ የመጡ ጥቆማዎች ብዛት |
| | | የምግብና የመድሃኒት ቁጥጥር የተደራሽነት አቅም ውስንነት | የቁጥጥር ዘርፉን መዋቅር አቅም በየደረጃው ማጠናከር | ምግ/መድ/ ቁጥ/፣ ክልሎች | የተሻሻለና በሰው ሃይል የተሟላ መዋቅር |
| | | ከባለድርሻ አካላት ጋር የተጠናከረ ቅንጅታዊ አሰራር አለመኖር | ቅንጅታዊ አሰራርን ማሻሻል | ምግ/መድ/ ቁጥ/ ባለስልጣን | የጋራ አሰራር መመሪያ ያለው የባለድርሻ አካላት ፎረም |
| 4.2 | ፈዋሽነታቸው ያልተረጋገጠ መድሃኒቶች በገበያ ውስጥ መኖራቸው ለህብረተሰቡ ጤና ጠንቅ መሆኑ | የኮንትሮባንድ ንግድን መቆጣጠር አለመቻል | በመግቢያና መውጫ ኬላዎች ቁጥጥር ማጠናከር | ምግ/መድ/ ቁጥ/፣ ክልሎች | የኮንትሮባንድ መቀነስ |
| | | | ከፍትህና ፀጥታ አካላት ጋር በቅንጅት መስራት | ምግ/መድ/ ቁጥ/ ባለስልጣን | በጋራ የተወሰዱ እርምጃዎች ብዛት |
| | | በአስመጪዎች በአከፋፋዮችና በመድሃኒት ቤቶች የሚደረግ ቁጥጥር አለመጠናከር | መደበኛና ድንገተኛ ቁጥጥሮችን ማጠናከር | ምግ/መድ/ ቁጥ/ ባለስልጣን | ቁጥጥር የተደረገባቸው ተቋማት ብዛት |
| 4.3 | በጤናና ጤና ነክ ተቋማት የሚሰጡ አገልግሎቶች ጥራትና ደህንነት መጓደል የህብረተሰብ ጤና አደጋ ስጋት እየሆነ መምጣቱ | የቁጥጥር ሥርዓቱ መዳከም | ግልጽ የሆነ የህግ ማዕቀፍ ማዘጋጀት | ጤና ሚኒስቴር | በሥራ ላይ የዋለ የህግ ማዕቀፍ |
| | | | ከባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሰራር ማጠናከር | ጤና ጤና ነክ ቁጥ/ ዳ/ሬት | የተፈጠረ የጋራ ፎረም |
| | | የአደረጃጀትና የሰው ሃይል ችግር | በፌዴራልና በክልሎች መዋቅሮችን ማደራጀትና የማስፈፀም አቅም ማጠናከር | ጤና ሚኒስቴር፣ ክልሎች | የተደራጀ መዋቅር |
| | | በየደረጃው የአመራሩ ትኩረት አናሳ መሆን | ተከታታይ ውይይቶችና የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራዎች | ጤና ሚኒስቴር | የተካሄዱ የውይይት መድረኮች ብዛት |
| | | የህብረተሰቡ ተሳትፎ አለመጠናከር | የንቅናቄ ሥራዎች መስራት | ጤና ሚኒስቴር | የተካሄዱ የንቅናቄ መድረኮች ብዛት |
| 5. የሰው ሃይልና የሀብት አስተዳደር | | | | | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 5.1 | በዘርፉ የሰው ሃይል ምደባ፣ ዝውውርና ጥቅማ ጥቅም ላይ የሚነሱ ቅሬታዎች መኖራቸው | ከክልል ክልል እንዲሁም በፌዴራል ተቋማት የአሰራር ልዩነት መኖር | የነጥብ ሥራ ምዘናና ሌሎች የጥቅማ ጥቅም መመሪያዎችን በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ ማድረግ | የሰው ሀብት አስ/፣ ክልሎች | በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ ያደረጉ ክልሎች ብዛት |
| 5.2 | የተጠየቁ ግዥዎች በወቅቱ አለመፈፀምና የጥራት ችግሮችም መኖራቸው | የሥራ ክፍሎች የግዥ ዕቅድ በወቅቱ አዘጋጅተው አለመላክ | የግዥ ዕቅድ ዝግጅት ላይ ለሥራ ክፍሎች ግንዛቤ መፍጠር | ፋይናንስና ግዥ | የግዥ ወቅታዊነትና ጥራት ላይ የተገልጋዮች እርካታ በመቶኛ |
| | | የግዥ ክፍል የሰው ሃይል እጥረትና የአቅም ውስንነት | የግዥ ክፍሉን አቅም ማጠናከር | ፋይናንስና ግዥ | |
| | | ከጥራት ይልቅ በዋጋ ማነስ ላይ ያተኮረ አሰራር መኖሩ | ለጥራት ተገቢውን ትኩረት መስጠት | ፋይናንስና ግዥ | |
| 5.3 | የግራንት ፋይናንስ አስተዳደር ላይ የሚታዩ ጉድለቶች ተጨማሪ ሀብት ለማሰባሰብ እንቅፋት መሆናቸው | ጠንካራ ክትትልና ድጋፍ አለመኖር | በየጊዜው የአፈፃፀም ክትትል በማድረግ ግብረ መልስ መስጠት | አጋርነትና ትብብር | የተደረገ ክትትልና ድጋፍ ብዛት |
| | | ክልሎችና ተቋማት የተላከላቸውን ሂሳብ አወራርደው በወቅቱ ሪፖርት አለማድረግ | ክትትል ማጠናከር፣ የተጠያቂነት አሰራር ማስፈን | አጋ/ ትብብር፣ ክልሎች፣ ተቋማት | የተወሰዱ የማስተካከያ እርምጃዎች ብዛት |
| 5.4 | የንብረት አያያዝና አጠቃቀም ላይ የሚታይ ብክነት በስፋት መኖሩ | የንብረት አስተዳደሩ ዘመናዊ አለመሆን | ዘመናዊ የንብረት አያዝያዝና አስተዳደር አሰራር መፍጠር | ን/አስ/ ጠቅላላ አገልግሎት | የተዘረጋ አሰራር |
| | | ሰራተኞች በግል ለወሰዱትና በጋራ ለሚጠቀሙት የተቋሙ ንብረት ጥንቃቄ አለማድርግ | የተጠያቂነት አሰራር መፍጠር | ሁሉም የሥራ ክፍሎች | የተወሰዱ የእርምት እርምጃዎች ብዛት |
| | | የህትመት ውጤቶችን ለታለመላቸው ዓላማ ባለማዋል የሚፈጠር ብክነት | ህትመትን መቀነስ፣ ከታተሙም ቶሎ ማሰራጨት | የሥራ ክፍሎች | ማዳን የተቻለ የብክነት መጠን በብር |
| 6. የጤና ፕሮግራሞች | | | | | |
| 6.1 | መከላከል በሚቻልባቸው በሽታዎች ለህመምና ሞት የሚጋለጥ በርካታ የህብረተሰብ ክፍሎች | የፕሮግራም ግብአቶች አቅርቦት መቆራረጥና እጥረት መኖሩ | የፕሮግራም ግብአቶች የፍላጎት ትንበያና የስርጭት አሰራርን ማሻሻል | መድ/አቅ/ኤጀ፣ መ/ህ/መ/ዳ/ሬት/፣ ክልሎች | የግብአት አቅርቦት መሻሻል በመሻሻል በመቶኛ |
| | | ተላላፊ ላልሆኑ በሽታዎች በቂ | ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች | በሽታዎች | የህመምና ሞት መቀነስ |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ትኩረት አለመስጠቱ | የመከላከልና ህክምናን ሥራዎችን ማጠናከር | መከ/መቆ/ ዳ/ሬት፣ ክልሎች | |
| | | በወረረሽኝ መልክ የሚከሰቱ በሽታዎችን በሚፈለገው ደረጃ መከላከል አለመቻል | ድንገተኛ የህብረተሰብ ጤና አደጋዎች የመከላከልና የመቆጣጥር አቅምን ማሳደግ | የህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት | በድንገተኛ አደጋዎችና በወረረሽኝ የሚከሰት የሞት ምጣኔ መቀነስ |
| | | የህብረተሰቡ ግንዛቤና አናሳ መሆን | የጤና ትምህርትና የህዝብ ንቅናቄ ሥራዎችን ማጠናከር | ህዝብ ግንኙነት፣ ጤና ኤክስቴንሽን | የህብረተሰብ ተሳትፎ መሻሻል |
| 7. የጤና መረጃ ሥርዓት | | | | | |
| 7.1 | ትክክለኛና የተሟላ መረጃን መሰረት ያደረገ የውሳኔ አሰጣጥ ላይ የሚታዩ እጥረቶች የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት እየጎዱ መሆናቸው | የሀሰት ሪፖርቶች መኖር | መረጃዎችን የማረጋገጥና የተጠያቂነት አሰራር ማጠናከር | ፖሊሲ ፕላን፣ ክልሎች | የመረጃዎች ተአማኒነት መሻሻል |
| | | ሪፖርቶች በወቅቱ አለመላክና የተሟላ አለመሆን | DHIS -2 አጠቃቀምን ማጠናከር | ፖሊሲ ፕላን፣ ክልሎች | የሪፖርቶች ወቅታዊነትና ምሉዕነት መሻሻል በመቶኛ |
| | | መረጃን በየደረጃው ለውሳኔ የመጠቀም ባህል አለመዳበር | የመረጃ አብዮት ትግበራን ማጠናከር | ፖሊሲ ፕላን፣ ጤና ኢንፎ፣ ክልሎች | መረጃ አጠቃቀም ላይ የታየ መሻሻል |
| | | ለውሳኔ የሚያግዙ የምርምር ሥራዎች በቂ አለመሆን | በጤና ሥርዓቱ ላይ የሚካሄዱ የምርምር ሥራዎችን ማሳደግ | ህብ/ጤ/ኢ/ ፣ አህሪ | የተካሄዱ የምርምር ሥራዎች ብዛት |

## 5. የአፈፃፀም አቅጣጫዎች

- ዕቅዱ በጤና ሚኒስቴር የሥራ አስፈፃሚ ከፀደቀ በኋላ በየደረጃው ተፈፃሚ ይሆናል
- ሁሉም ተቋማትና ክልልች ይህንን ዕቅድ እንደ መነሻ በመውሰድ ከራሳቸው ነባራዊ ሁኔታ ጋር የተጣታመና የድርጊት መርሃ ግብር ያለው ዝርዝር የመልካም አስተዳደር ዕቅድ ማዘጋጀት ይጠበቅባቸዋል፡፡ የሁሉም ተቋማት ዕቅድ በተቋማቱ ማኔጅመንት ኮሚቴ መጽደቅ ይኖርበታል፡፡
- በሁሉም ተቋማት የሚገኙ የሥራ ክፍሎች የየራሳቸውን የመልካም አስተዳደር ዕቅድ ያዘጋጃሉ፡፡ የሥራ ክፍሎች የመልካም አስተዳደር ዕቅድ ከአመታዊ ዕቅዳቸው የተለየ ሳይሆን በመደበኛ ዕቅድ ከያዟቸው ሥራዎች ጋር በማስተሳሰር ወደ መልካም አስተዳደር ቅኝት በመቀየር የሚታቀድ ይሆናል፡፡
- በየደረጃው ያለው አመራር ለመልካም አስተዳደር ዕቅድ ዝግጅትና ትግበራ ትኩረት ሰጥቶ መከታተልና መደገፍ ይጠበቅበታል፡፡

## 6. የክትትልና ድጋፍ ሥርዓት

- የሪፎርምና መልካም አስተዳደር መዋቅሮች የየተቋማቸውን የመልካም አስተዳደር ዕቅድ ዝግጅትና የትግበራ ክትትል ያስተባብራሉ
- በሁሉም ተቋማት በየወሩ የመልካም አስተዳደር ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ለማኔጅመንት ቀርቦ ይገመገማል
- ተጠሪ ተቋማትና ክልሎች በየሩብ አመቱ የተጠቃለለ የመልካም አስተዳደር አፈፃፀም ሪፖርት ለጤና ሚኒስቴር ይልካሉ፡፡ የጤና ሚኒስቴር ሪፖርቶችን በመገምገም የጽሑፍ ግብረ መልስ ለሁሉም ይልካል
- የጤና ሚኒስቴርና የተጠሪ ተቋማት የሪፎርምና መልካም አስተዳደር ፎረም በየወሩ በመገናኘት ሥራዎችን በጋራ ይገመግማል
- የጤና ሚኒስቴር፣ የተጠሪ ተቋማትና የክልል ጤና ቢሮዎች የሪፎርምና መልካም አስተዳደር መዋቅሮች ግምገማዊ በየስድስት ወሩ ይካሄዳል